የሚስጥራዊ መረጃ መግለጫ (Confidential Information Declaration)

*<u>መመሪያዎች</u>*

**ለችሎቱ ሰነዶችን ለዳኛው ማስገባት ከፈለጉ ይህን ቅጽ ሞልተው ከሰነዶችዎ ጋር መላክ አለብዎት። ሁሉም የቀረቡት ሰነዶች በሌላኛው ወላጅ፣ የጉዳዩ ወገን እና/ወይም ወኪላቸው ሊታዩ ይችላሉ።**

የግዛት ህግ በእርስዎ የልጅ ድጋፍ ጉዳይ ላይ ያሉ አንዳንድ መረጃዎች ለሌላ ወላጅ፣ ለጉዳዩ ወገን እና/ወይም ተወካይ እንዳይለቀቁ ይጠብቃል። እርስዎ ካልተስማሙ በስተቀር ስለ አካባቢዎ መረጃ ሊጋራ አይችልም። ይህ መረጃ “መገኛን የሚገልጽ መረጃ” ይባላል። የመኖሪያ ቦታዎን፣ ሥራዎን እና እርስዎን ወይም የልጅዎን ትምህርት ቤት ያካትታል። ይህ በአንዳንድ ጉዳዮች ወይም ሁኔታዎች ላይ የማድባት፣ የቤት ውስጥ ጥቃት ወይም የአካል ደህንነት አደጋዎችን ለመከላከል እንዲያግዝ ነው። ሰነዶቹ ለሌላኛው ወላጅ፣ የጉዳዩ ወገን እና/ወይም ወኪሎቻቸው እንዲጋራ የማይፈልጉትን ሌሎች ሚስጥራዊ መረጃዎችን ሊይዙ ይችላሉ።

**መገኛን የሚገልጹ ወይም ሌላ ሚስጥራዊ መረጃ ያላቸውን ሰነዶች ከማቅረብዎ በፊት፣ ለሌላኛው ወላጅ፣ ለጉዳዩ ወገን እና/ወይም ወኪሎቻቸው እንዲጋራ የማይፈልጉትን ማንኛውንም መረጃ ማስወገድ ወይም ማሻሻል (ማጥፋት) አለብዎት።** <u>ይህ መረጃ በግዛት ህግ የተጠበቀ ነው። ለጉዳዩ እስካልፈለገ ድረስ መወገድ አለበት።</u> አንዳንድ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- እንደ የእርስዎ የማህበራዊ ዋስትና ቁጥር እና የባንክ ሂሳብ መረጃ ያሉ በግል ሊለይ የሚችል መረጃ።
- ስለ ትምህርት ቤት፣ የህጻናት መዋያ እንክብካቤ አቅራቢዎች፣ የህክምና አቅራቢዎች ወይም አሰሪዎች ማንኛውም ሊለይ የሚችል መረጃ።
- የደብዳቤ መላኪያ እና አካላዊ አድራሻዎች (የተለያዩ ከሆነ)።
- ማንኛውም የጤና ሁኔታ/መረጃ (አካላዊ ወይም አዕምሯዊ)።
- የሚገኙበትን አካባቢ የሚገልጽ ማንኛውም የግዛት፣ የከተማ ወይም ካውንቲ ማጣቀሻ።

የአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ (Office of Administrative Hearings, OAH) ምንም አይነት መረጃ አያሻሽልልዎትም።

*መግለጫ*

በWashington የተሻሻለው ኮድ (Revised Code of Washington, RCW) 26.23.120(7) ላይ ያለኝን የሚስጥራዊነት መብቴን በመተው በዚህ ጉዳይ ላይ አሁን ወይም ወደፊት በማንኛውም ጊዜ ባቀረብኳቸው ሰነዶች ውስጥ ያለውን መረጃ ሌላኛውን ወላጅ ጨምሮ፣ ሌሎች ወገኖች እንዲያዩ OAH እንዲፈቅድ ፈቃዴን ሰጥቻለሁ። ሰነዶችን ለOAH ከማቅረቤ በፊት፣ ለሌላኛው ወላጅ ጨምሮ ለሌሎች ወገኖች ማጋራት የማልፈልገውን ሁሉንም መረጃ ማሻሻል (ማጥፋት) የእኔ ኃላፊነት እንደሆነ ተረድቻለሁ።

እነዚህ ሰነዶች ለሌላኛው ወላጅ፣ ለጉዳዩ ወገን እና/ወይም ወኪላቸው ምንም ተጨማሪ ማሻሻያ ሳይደረግላቸው ሊታዩ እንደሚችሉ ተረድቻለሁ። ሌላኛው ወላጅ፣ የጉዳዩ ወገን እና/ወይም ተወካያቸው እንዲያዩት የማልፈልገውን ሁሉንም መረጃ አሻሽያለሁ (አጥፍቻለሁ)። እነዚህን ሰነዶች ለOAH በማቅረብ፣ ምንም ያልተሻሻለ መገኛን የሚገልጽ መረጃ እና ሌሎች በWashington አስተዳደራዊ ኮድ (Washington Administrative Code, WAC) 388-14A-2105 እና WAC 388-14A-2107 ጥበቃ የሚደረግላቸው ሌሎች ሚስጥራዊ መረጃዎችን OAH እንዲለቅ እንዲሁም በእነዚህ ደንቦች መሰረት የተሰጡኝን የሚስጥራዊነት መብቶችን እንዲያስቀር እፈቅዳለሁ።

የታተመ የፓርቲ/የወላጅ ስም

የፓርቲ/የወላጅ ፊርማ

**ፈቃድ የተሰጣቸው ተወካዮች፡-**

እኔ የምወክለው ወገን እነሱን ወክዬ እነዚህን ሰነዶች ሳልሰርዛቸው እንዳቀርብ ፈቃድ እንደሰጡኝ አረጋግጣለሁ።

የተፈቀደለት ተወካይ የታተመ ስም

የተወካዩ ፊርማ

**ይህን ቅጽ መሙላት አለመቻልዎ ሰነዶችዎ በOAH ውድቅ እንዲደረጉ እና ለተጨማሪ እርምጃ ወደ እርስዎ እንዲመለሱ ሊያደርግ ይችላል።**